# ኣሸማቅቆ የማሸመድመድ ስልት

**ኣስተያየት**

ገብረ ሥላሴ ኣርኣያ (ሰኔ 2009 ዓ.ም)

ሀ፡- በትግራይ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ከሚያወሩት በተቃራኒው መሆኑን ጠንቅቀው ቢያውቁም ትግራይ በልማት ልትሰምጥ ነው እያሉ ቀጣይነት ያለው ፕሮፓጋንዳ በማካሄድ የትግራይ ፖለቲከኞችን ኣሸማቅቆ በክልሉ የሚደረገውን የልማት ጥረት የማስተጓጎል ኣካሄድ እንደ ስልት ተይዞ ለኣመታት ተሰርቶበታል። ይህ ለ27 ኣመታት ብሰፊው የተሰራበት የማሸመድመድ ስልት የመሪዎቻችን ልብ ሰርስሮ በመግባቱ ዛሬ ፍሬ ኣፍርቶ ትግራይን ጎድተዋል። የትግራይ መሪዎች የተወራውን ልማት እውነት ሆኖ ቢገኝ የሚያስጠያቃቸው ይመስል ከፌደራል መንግስት ለክልሉ የሚገባ ጥቅም ኣላስከበሩም ብቻ ሳይሆን በተመደበላቸው ባጀትም ተገቢ ልማት ባለምስራታቸውም ጭምር ክልሉ በልማት ወደ ኃላ ቀርቷል። የክልሉ በልማት ወደ ኃላ መቅረት፣ በክልሉ ያለውን የተበላሸ ቢሮክራሲያዊ ኣሰራርና ያልተመጣጠነ ግብር ማስከፈል ብክልሉ ሊፈጠር የሚገባውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በተገቢ መንገድ ለማስኬድ ኣልተቻለም። በመሆኑም ነጋዴው ወደ ኣዲስ ኣበባ፣ ወጣቱ ወደ ስደት፣ ስራ ኣጥነት ከፍተኛው ቁጥር፣ ከኣምስት ኣመት በታች ህፃናት ሞት ኣፋርን ብቻ የበለጠች፣ ከ43 በመቶ በላይ ህዝብ በሴፍቲኔት እህል እርዳታ የሚኖር፣ በልመና የሚተዳደር ህዝብ ከፍተኛውን ቁጥር ያላት፣ የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት የበዙባት፣ ከየትኛውም ክልል የበለጠ በጥላ ስር የሚማሩ ህፃናት ያሉባት፣ ከእንስሳ ጋር እየተጋፋ ውሃ የሚጠጣ ህዝብ በብዛት ያላት፣ ከፌደራል ፕሮጀክቶች ሆን ተብሎ የተነጠለች ወይም ”የምትቀጣ”፣ ከፌደራል የገንዝብ ተቋማት ለግብርና ኢንቨስተሮች ዝቅተኛው የባንክ ብድርና የመድን ዋስትና የሚሰጥባት፣ ሰላምና ጦርነት ባልሆነበት ሁኔታ በምልሻና በጦር ሰራዊት ስር የምትኖር፣ ብጸጥታ ስጋት ምክንያት በድምበር ነዋሪ የሆነውን ግማሹ የክልሉ ህዝብም ኣገራዊ ሃላፊነት ተሸክሞ የኖረና ያለ ነገር ግን ከፌደራል መንግስቱ ምንም ኣይነት የልማት ኣማራጭ ሳይቀርብለት በስጋት የሚኖርባት ክልል ሆናለች። ነገር ግን ከምትሰበስበው በኣገሪቱ ከፍተኛው የሚባለውን ግብር እና የምታስገኘውን የውጭ ምንዛሬ ያስተዋሉ ወገኖች ትግራይ ለፌደራል መንግስቱ ኣንድ ሚሊዮን ሰጥታ ኣስር ብር የምትቀበል ክልል ነች በማለት ይገልጹታል። ይሁን እንጂ ህዝቡ እስከ ኣሁን ዝምታን መርጦ ቆይቷል። በእርግጥ ኣይቀጥልም።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ይሉ ደግሞ ትግራይ ኣስጠግታ ያሳደገችውን ብኣዴን በውስጡ የበቀለው የትምክህት ሃይል የበላይነቱን ኣግኝቶ ከህዝባዊ መስመሩ በመውጣት ከታሪካዊ ጠላቶችዋ ጋር በማበር ትግራይን እና ህዝቧን በጠራራ ፀሃይ ደፍረዋል፣ ገድሏል፣ ኣስገድሏል፣ ኣስዘርፈዋል፣ ኣፈናቅሏል፤ ከክልሉ ኣባረዋል፣ ለስደት ዳርገዋል፣ ለደረሰው ጉዳትም ተገቢ አውቅና እንደመስጠት በመገናኛ ብዙሃን ሳይቀር ከደዋል ወይም ኣጣጥሏል። ከዚህ ጉዳት በተጨማሪ በውጭ እና በውስጥ ሆነው በትግራይ ህዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ያወጁ ፀረ ብዙህነትና ሃሳዊ የኣንድነት ጠበቆች የሚያራምዱትን መሰረት የሌለው ፕሮፓጋንዳ እንዳለ በመቀበል የትግራይ የበላይነት ኣለ የሚል ኣቋም በማራመድ እና በገሃድ ስም የማጥፋት ዘመቻ ከከፈቱ ቆይቷል። እንዲሁም ትግራይ ከማንም በላይ ለምታለች ብሎ በማስወራት የተሰራ መንገድ፣ ፎቅ፣ በፌደራል ተቋማት ያለ ሹመኛ ወዘተ በመቁጠር ህዝቦች በጥርጣሬ ኣይን የሚያዩዋት ክልል ተደርጋ እንድትታይ ቀጣይና ኣደገኛ የሆነ ጥረት ኣድርገዋል። እነሱም ከስርኣቱ ተጠቃሚ ሆኖው ሳለ ኣልተጠቀምን በሚል ሌላው ህዝብ የራሱን ትቶ በትግራይ ህዝብ ላይ እንድያቶኩር እና በጠላትነት እንዲመለከተው ሆን ተብሎ የተቀየሰ ስልት ይዘው ይንቀሳቀሳሉ። ’’ብልጥ ልጅ እየበላ ያለቅሳል” በሚል መርህ እየተመሩ ሌሎችን በማሸማቀቅና በማዳከም በኢኮኖሚውንም ሆነ በፖለቲካው ዘርፍ ድሮ የነበረውን የበላይነታቸውን ማረጋገጥ ብሎም ኢትዮጵያን ከመፍረስ የታደጋት የፌደራል ስርኣትን ኣፍርሶ ሌሎችን የሚጨፈልቅ ኣሃዳዊ ስርኣተ መንግስት መፍጠር ኣላማ ኣድርገው ይንቀሳቀሳሉ ቢባል የተጋነነ ኣይሆንም። ይህ ለማስካት ሲሉም ራሳቸው ተቆጣጥረውት የነበረና ያለ የመንግስት መዋቅር መጀመሪያ ማመጣጠን በሚል፣ ከዛም ስልጣን ኣነሰን፣ ቀጥሎም ሁሉም የፌደራል ስልጣን እና ወሳኝ ቦታ የትግራይ ተወላጅ ብቻ እንደያዘው ኣድርገው በማስወራት ህወሓት ላይ ብቻ ሳይሆን የትግራይ ህዝብ ላይ ከዘመቱበት ቆይቷል።

ለ፡- ኢህኣደግ ደርግን ሲገረስስ የኢህኣደግ ሰራዊት በኣብዛኛው የህወሓት ታጋይ እንደነበር ይታወቃል። ሆኖም ሁሉም ብሄሮች በእኩልነት የሚሳተፉባት ኢትዮጵያን ለመፍጠር ከነበረው ፅኑ እና ቀና እምነት ኣብዛኛው የህወሓት ታጋይ ካለምንም የጥሮታ ገንዘብ እና ጥቅማጥቅም ወደ ቀየው ተመልሶ ንሮውን እንዲገፋ ተደርገዋል። ከዚህ ከተሰናበተው ታጋይ ቀላል የማይባል መንገድ ላይ ወደቀ፣ ተራበ፣ በበሽታ ተጠቅቶ ኣሳካሚ ኣጥቶ ሂወቱ ኣለፈ፣ ለህዝብ እና ለኣገር ሲሉ የሚወልዱበት እና የሚማሩበት ጊዜ በረሃ ለበረሃ ሲንከራተቱ ያሳለፉ ሴት ታጋይም ረዳት ኣጥተው እጅግ ኣሳዛኝ እና ኣሳፋሪ ሁኔታ ላይ ወድቀው ቀርቷል። ኢፍትሃዊነቱ በዚህ ኣላበቃም። ከዚህ በላይ የሚያሳዝነው እነዚህ ፍትሃዊ ባልሆነ ሁኔታ ከሰራዊቱ የተሰናበቱ ታጋዮች ሻዕቢያ በወረረን ጊዜም ወደ መከላከያ ሰራዊቱ እንዲመለሱ ተጠይቀው ኣዎንታዊ ምላሽ በመስጠት ቀላል የማይባሉ ታጋዮች የሂወት እና የኣካል መስዋእት ከፍሏል።

በመከላከያ ሰራዊት የቀሩትም ጥቂት ሰራዊት(ታጋይ) ከነበራቸው የብኣዴን፣ ኦህዴድ እና የደቡብ ህዝቦች ድርጅት በመኣርግ እና ሃላፊነት ለማመጣጠን ሲባል ረጅም ልምድ ያላቸው የህወሓት ታጋዮች ከነበሩበት የሃላፊነት ደረጃ በሁለት እርከን ዝቅ ብለው መኣርግ እንዲሰጣቸው መወሰኑንና መተግበሩን ይታወቃል። የኣንድ ኣገር የመከላከያ ሰራዊት በብሄር የተመጣጠነ እንዲሆን ማድረጉ በጣም ትክክለኛ ፖለቲካዊ ውሳኔ ሲሆን በብቃት ሊሰጥ የሚገባው ወታደራዊ መኣርግ ግን በብሄር ሲከፋፈል በኣለም የጦር ሰራዊት ታሪክ የመጀመሪያው መሆን ኣለበት። ይህም ሆኖ በሰራዊቱ ሌሎችን "የማብቃት ስራ" እየተሰራ በትግሉ ወቅትና በመከላከያ ሰራዊቱ ሰፊ የወታደራዊ ልምድ ያላቸው ወታደራዊ መኮንኖች ገና ማገልገል በሚችሉበት እንድሜ እያሉ ከሌላ ብሄር ለሚመጡ መኮንኖች ቦታ እንዲለቁ እየተደረገ ቆይቷል ኣሁንም ቀጥሏል። የብሄር ማመጣጠን ስራ እየተሰራ እንደሆነና በወቅቱ የነበረውን የሰራዊት ብዛት ትልቁ ቁጥር የሚይዘው የኣማራ ብሄር ተውላጅ፣ 2ኛ የኦሮሞ፣ 3ኛ፣ የደቡብ፣ 4ኛ የትግራይ መሆኑን እና በላይኛው ኣመራርም በተመሳሳይ መልኩ የማመጣጠን ስራ እየተሰራ እንደነሆን የመከላከያ ሚንስትሩ ኣንድ ወቅት በኢቢሲ ቀርበው ማብራሪያ መስጠታቸው ይታወሳል።

እውነታው ከላይ እንደጠቀሰው እያለ ህወሓትን እና ማህበራዊ መሰረቱ የሆነውን የትግራይ ህዝብን ኣክርረው በሚጠሉ ሃይሎች፣ በተለይም በጦርነቱ እና በራሳቸው የፖለቲካ ይዘት ምክንያት የተሸነፉት የደርግ ትርፍራፊ፣ የኢህኣፓ እና ሌሎች የቂም ሃይሎች ባወጁት የማያባራ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ጉዳዩ ባልገባቸው ወገኖች ዘንድ የተዛባ ኣመለካከት እንዲይዙ ምክንያት ሆነዋል። ይህ በተራ ዜጎች ብቻ ሳይወሰን በኢህኣደግ ኣባል ድርጅቶችም፣ በተለይም በኣሁን ግዜ የኣማራ ክልል እየመራ የሚገኘው ብኣዴን የዚህ የቂም ሃይሎች የሚበትኑትን በሬ ወለደ ፕሮፓጋንዳ ሰላባ በመሆን በሂደት ከህዝባዊ መስመሩ ኣፈንግጦ የጥፋት ሃይሉን ተቀላቅሏል (ኣመራሩ ውስጥ ጥቂት ቀና ሰዎች፣ ነገር ግን ሃይል የሌላቸው ኣሉ)። በመሆኑም ላለፉት ኣመታት ከነዚህ የጥፋት ሃይሎች ያበረው ድርጅት በክልሉ ባለው ሙሉ ህገመንግስታዊ ስልጣን እና ድርጅታዊ ነፃነቱን ተጠቅሞ ቀላል የማይባሉ የድርጅቱ ኣባሎችና በኣገሪቱ የሚገኙ ተከታዮች የዚህ የተሳሳተ ኣመለካከት ሰለባ በማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጥፋት ሃይሎቹን ኣገልጋይ ለመሆን ብቅተዋል። ይህ በቂም ሃይሎች የተንበረከከው ሃይል ህዝባዊ መስመሩን ስቶ ወደ ጸረ ብዙህነት ካምፕ ከተቀላቀለ ጀምሮ የሚያስተዳድረው ክሉል ለጥፋት ሃይሎች ማንቀሳቀሻ ክፍት በማድረግ በክልሉ በሚኖሩት የሌላ ብሄር ተወላጆች ላይ ዘግናኝ ጥቃት እንዲፈፀም ኣድርገዋል። ኣምና ብቅማንት እና በትግራይ ብሄር ተወላጆች የወሰደውን ኣሳዛኝ ጥቃት ፍትህ ባይገኝለትም ጥቁር ታሪክ ሰንዶ ኣልፈዋል።

ሐ፦ ሰው በላውን የደርግ መንግስት በኢህኣዴግ መንግስት ይተካ እንጂ በፌደራል መንግስት የሚገኘው መንግስታዊ መዋቅር ከላይ እስከታች የተሞላው በደርጉ ዘመን ሲያገለግሉ የነበሩ እና ኢህኣዴግን (በተለይም ህወሓትን) የማይቀብሉ ቢሮክራቶች በብዛት በመኖራቸው ኣዲሱ መንግስት ፖሊሲ በማስፈፀም ላይ ከባድ እንቅፋት ሆነውበት በመቀጠል ኢህኣዴግን የሚጠላ ህዝብ እንዲበራከት ምክንያት ሆነዋል። ይሄንን ለማሻሻል በማሰብም የኢህኣዴግ ኣባል ድርጅቶች በቀድሞው መንግስት ኣገልጋይ የነበሩ ቢሮክራቶችን የየብሄር ድርጅቱ ኣባል ኣድርገው ቢመለምሉዋቸውም በኣላማ እምነት እና ህዝብን በማገልገል ስሜት ባለመሆኑ ኣባልነታቸው ለኪራይ ሰብሳቢነት እና ኣባል የሆኑበትን መንግስት ለመጣል የተጠቀሙበት ብዙ ናቸው። ቅንጅት የዛ ውጤት ነበር።

ይህ የኪራይ ሰብሳቢ መንጋ ከፀረ ብዙህነት እና የቂም ሃይሎች እንዲሁም የኢህኣዴግ ኣባል ድርጅቶች ከሚመለምሏቸው የኣላማ ሽታ ያልነካቸው ኣባላት ጋር በመመጋገብ ኣባል የሆኑበትን ድርጅት ውስጡን ከማዳከም በዘለለ በኣባል ድርጅቶች መካከል ጥርጣሬ እና ያለመተማመን እንዲነግስ ሳይታክቱ ሰርቷል ብቻ ሳይሆን ብኣዴንን የመሰለ ድርጅትም ጠልፈው ለመጣል በቅቷል። ሆኖም ብእዴን ከህዝባዊ እምነት ወጥቶ ዘር ለማጥፋት ከተነሱ ፅንፈኛ ሃይሎች ጋር በማበር በክልሉና በኣጎራባች ወረዳዎች የፈጸመውና ያስፈጸመው ጸረ ህዝብ ተግባር ዓባይ ወንዝን እንደማያሸግረው ሲገነዘብ በፌደራል ተቋማት የያዘውን ስልጣን (ከድሳ ፐርሰንት በላይ) በመጠቀም በኣገሪቱ ፖለቲካና ኢኮኖሚ የበላይነት ኣላቸው ብሎ የፈረጃቸው ህወሓት፣ ትግራይን እና የትግራይ ተወላጆችን ለማሽመድመድ ሌት ተቀን እየሰራ ይገኛል። ይህ እየሆነ ያለው በጥልቀት በመታደስ ላይ ነን የሚል ዲስኩር ባላቋረጠበት ሁኔታ እንደሆነ ልብ ይለዋል።

***ይህ ሁሉ ግን ለምን?***

የትግራይ ህዝብ በኣረመኔዎቹ እና በኣድላዊ ስርኣቶች ተማርሮ የትጥቅ ትግሉን በማፋፋም ከመቶ ኣመት በላይ የቆየውን ግፍኛ የነፍጠኞች ስርኣት ለመገርሰስ በተደረገ የትንቅንቅ ፊልሚያ እና ኣንፀባራቂ ድል የኣንበሳውን ድርሻ የተጫወተ በመሆኑ ከተሸናፊው ሃይል የሚሰነዝር ቂም የከረረ ኣድርጎታል። እነዚህ ሃይሎች ኣሁን ላሉበት የማይወዱት ሁኔታ ህወሓት እና የትግራይ ህዝብን ተጠያቂ ያደርጉታል። በመሆኑም እነዚህ የተሸነፉ ሃይሎች ኢህኣዴግ ውስጥ ከመሸገው ተንበርካኪ ሃይል ጋር በመሆን በተለያዩ ዘዴዎች ትግራይን እና ህዝቧን ለማሽመድመድ ሌት ተቀን እየሰሩ ይገኛሉ። የትግራይ ህዝብ ያልሆነውን ሆነ እያሉ በማጠልሸት በሌሎች ኢትዮጵያዊያን ዘንድም እምነት እንዲያጣ እየተጉ ነው። ሆኖም እነዚህ በእኩልነት መኖር ያልተዋጠላቸው ሃይሎች በሌሎች ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ላይ ካላቸው ታሪካዊ ንቀትና ሸውራራ እምነት በመነሳት ትግራይን በማሽመድመድ ብቻ የፈለጉት ማሳካት የሚችሉ ኣድርገው ያስባሉ። ይህ ግን ስህተት መሆኑን ብቻ ሳይሆን ሊሆን የሚችለውን እና የሚጋጥማቸውን ኣደጋ መረዳት ይችሉ ዘንድ እቅጩን ሊነገራቸው ይገባል። እንግዲያውስ ትግራይን በማሽመድመድ የሚያተርፉት ነገር ቢኖር ኣንድ ነገር ብቻ ነው፦ በዚህ ፀረ ህዝብ እና ፀረ ብዙህነት ተግባራቸው ምክንያት ከሌሎች ክልሎች እና ብሄብሄረ ሰቦች እምነት ማጣት ይሆናል። የቅርብ ምሳሌ ለማስታወስ ያክል፣ ኣምና በኣማራ ክልል በትግራይ ህዝብ ላይ የደረሰው ጭፍጨፋ ክልሉ በጥርጣሬ ኣይን ሊታይ እንዳደረገው እና ከሌላ ክልል የተመደቡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ወደ ኣማራ ክልል ኣንሄድም እስከማለት የተደረሰበት ሁኔታ

ኣይተናል። በክልሉ ይሰሩ የነበሩ የትግራይ እና የሌላ ብሄር ተወላጆችም ክልሉን ለቀው የሄዱበት ሁኔታ ነው ያለው። ተመሳሳይ ጥቃት የደረሰባቸው የክልሉን ግማሽ መሬት የያዙት የቅማንት ብሄርም የራሳቸው ኣስተዳደር፣ የኣገው ህዝብም የራሱ ክልል የማቋቋም ጥያቄ እስከ ማቅረብ ደራሷል። ”ዛሬ ብትግራይ ላይ ነገ ድግሞ በኛ ላይ የታወጀ የጥፋት መንገድ ነው” ብለው ራሳቸውን ለመከላከል የተዘጋጁ ክልሎች እንደነበሩም ታዝበናል። የዚህ ውጤት ደግሞ ኣብሮ የመኖርን እድል ተመናምኖ እስከ መበተን የሚሄድ ኣደጋ ሊፈጠር እድሉ ሰፊ ያደርገዋል። ኣያድርስና ይህ ቢያጋጥም ግን እንደ ኩርዶች ኣምስት ቦታ የሚበተኑ እነርሱ እንደሚሆኑ ጥርጥር የለውም፥ ይብላኝ ልሚስኪኑ ገበሬ።

***መፍትሄው***

የኢህኣዴግ ኣባል ድርጅቶች በውስጣቸው ያለውን ኣጥፊ ሃይል ነቅለው የማውጣት ወኔ እንደሌላቸው ኣይተናል። ጥልቅ ተሃድሶ ብለው ጥልቅ ብልሽት ውስጥ እንደገቡ እያየን ነው። ኣገሪቱ የዘመነ መሳፍንቱ ኣይነት ሁኔታ ልትገባ ምንም ኣልቀራትም። ኣሁን ባለበት ሁኔታ ከቀጠልን ኣገሪቱ ኣይታው የነበረውን የተስፋ ጭላንጭል ጨልሞ ወደ መበታተን የማንደርስበት ምክንያት ኣይኖርም። መበታተን ደግሞ ሁሉንም የሚጎዳ ቢሆንም በበለጠ በዘላቂነት የሚጎዱ ግን ይኖራሉ። ኣያድርስ። ይህ እንዳያጋጥም ከተፈለገ የኢህኣዴግ ኣባል ድርጅቶች የሚከተለውን ማድርግ ይኖርባቸዋል።

፩ኛ፡- እያንዳንዱ የኢህኣዴግ ኣባል ድርጅት ውስጡን ካላጠራ ኣባል ድርጅቱ ከኢህኣዴግ ተሰናብቶ በፌደራል ተቋማት ያለውን ወንበር፣ የህዝብ ውክልና እና ክልሉን የማስተዳደር ስልጣን እስከ የሚቀጥለው ምርጫ ብቻ ጸንቶለት ይቀጥላል። ያኔ እንደ ማነኛውም ድርጅት በግሉ ይወዳደራል። የኢህኣዴግ ኣባል ድርጅቶች ሁሉም ኣሳሳቢ የሆነ ውስጣዊ ብልሽት ቢኖራቸውም የብኣዴንን ብልሽት የሚስተካከል ስለሌለ ያለው ኣማራጭ ከፀረ ህዝቦች ጋር የፈጠረውን ኣዲስ ጋብቻ መፋታት ወይም ማህበሩን መልቀቅ ይኖርበታል።

፪ኛ፡- ኣጋር እየተባሉ የሚጠሩ የተለያዩ ክልሎች እየመሩ ያሉትን ድርጅቶች የኢህኣዴግ ኣባል በማድረግ በኣገሪቱ የፖለቲካ ሂደት ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ። ኣንዳንዶቹ ከኢሃዴግ ድርጅቶች የበለጠ ህዝባዊነት የተላበሱ እንደሆኑ ይታወቃል። በጎንደር የቅማንት እና የትግራይ ህዝብ ሲጨፈጨፍ ብኣዴን የደረሰው ጉዳት ተጋኖዋል በማለት ሽምጥጥ ኣድርጎ ሲክድ የሱማሌ እና ሌሎች ክልሎች ግን በኣደባባይ በመውጣት ህዝባዊነታቸውን ኣስመክረዋል። ሌላው ኣጋር ድርጅቶች በሙሉ ማለት ይቻላል ብዙሃነትን በሙሉ ልብ የሚቀበሉ ናቸው። ከኣንዳንዶቹ የኢህኣዴግ ኣባል ድርጅቶች የተሻል ህዝባዊነት እያላቸው እና የኢህኣዴግን ፖሊሲ በተሻለ ሁኔታ ኣስፈፃሚ ሆነው እየሰሩ ባለበት ሁኔታ ኣባል የማይሆኑበት ኣሳማኝ ምክንያት ኣይኖርም። ስለሆነም እነዚህ ሃይሎች ወደ ኢህኣዴግ በማስገባት በኣገር ደረጃ (በሁሉም የፌደራል ተቋማት) ያላቸው ተሳትፎ ከፍ ማድረግ የግድ ይላል። ይህ ኣሁን በኣባል ድርጅቶች መካከል ያለውን ፉክክር እና ጎታች ፖለቲካ በኢህኣዴግ ምክርቤት፣ በሚኒስትሮች ካቢኔ፣ እና በተለያዩ የፌደራል ተቋማት ውስጥ የፖለቲካ ተዋናዮችን በመጨመር ያለውን ኣሳሳቢ ሁኔታ የሚሻሻልበት ዕድል መፍጠር ይቻላል።

፫ኛ፡- የኣገሪቱ ዘላቂ ዋስትና የፌደራል ስርኣቱ ኣጠናክሮ መቀጠል ብቻ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። መታወቅ ያለበት ቢኖር የጥፋት ሃይሎች የያዙትን እኩይ ኣላማ እንዳይሳካ ያደረገው የፌደራል ስርኣቱ መኖሩ እንጂ ለኣርበኞች ግንቦት ሰባት ድርጅት የመንግስትን ሚስጥር በሚያቀብሉ ባለስልጣናት የተሞላው የኢህአዴግ መንግስት ጥንካሬ ኣይደለም። ስለዚህ የፌደራል ስርኣቱ ኣጠናክሮ መቀጠል ኣማራጭ የሌለው መፍትሄ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። በመሆኑም የፌደራል ተቋማት በጥፋት ሃይሎች እጅ ወድቀው ኣገር ኣቀፍ ችግር እንዳያስከትሉ ከተፈለገ ለኢህኣዴግ ኣባል ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን በ”ኣጋር” ድርጅቶች የሚመሩ ክልሎችም በፌደራል ተቋማት ውስጥ በቂ ቦታ በመስጠት የብሄር (ከኣቅም ጋር) በስልጣን የማመጣጠን ስራ በፍጥነት መሰራት ይኖርበታል። እንደሱ ከሆነ የፈለገው ቢንፈራገጥ የክልሉን ወንዝ ተሻግሮ የሚያንበረክከው ክልል የለም፣ የሚያፈርሰው ስርኣትም ኣይኖርም። ኣምና ብኣዴንን በጠልፉ ቡዱኖችና ግብረ ኣብሮቻቸው የሞከሩት ዘር ተከል የጥፋት ዘመቻ ኣዋሳኝ ወንዞች ሊሻገር ያልቻለ ኣንድ ማሳያ ነው። በእርግጥ የሚቀበላቸው ኣጡ እንጂ ጎንደር ላይ የፈጠሩት የወልቃይት ኮሚቴ እና የኦሮሚያ ነውጥም ለኣጋርነት በመጥለፍ ወንዝ መሻገሪያ ሊያደርጉዋቸው እንደሞከሩ ይታወቃል። ይህንን ኣሰቃቂና የማይሳካ ሃቅ የገባቸው የጥፋት ሃይሎች ኣሁን እንደ ኣማራጭ የወሰዱት የፌደራል ስርኣቱን መዘውር የሆኑት የፌደራል ተቋማት በወሳኝ መልኩ መቆጣጠር እና መሰሪ ተግባራቸው (ስርኣቱን ማፍረስ) በተለያየ መንገድ ለማስቀጠል እየሞከሩ ይገኛሉ። ስለሆነ የፌደራል ተቋማት በኣንድ ብሄር እጅ እንዳይወድቁ ወሳኝ ስራ መሰራት ይኖርበታል። ከዚህ ጎን ለጎንም ህገመንግሥቱ በኣግባቡ ይፈጸም ዘንድ የህግ ኣውጪው በህግ ኣስፈፃሚው ኣካል ሳይሸማቀቅ ትርጉም ባለው ሁኔታ ኣስፈፃሚውን ኣካል የመቆጣጠር ስራ መስራት ይኖርበታል።

፬፡- በኣገሪቱ የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ ከኣፍ ያለፈ በተግባር ማሳየት የግድ ይላል። ለኣገሪቱ ህልውና ሲባል ወንጀል የፈጸሙ ትልልቅ ባለስልጣኖች ወደ ህግ ለማቅረብ ኣባል ድርጅቶች ወኔው ሊኖራቸው ይገባል። ኣምና በኣማራ ክልል እና በኦሮሚያ ክልሎች የተፈጠረው ኣመፅ ሁሉም የኢህኣዴግ ድርጅቶች ራሳቸውን በመገምገም ’ጻረ ዴሞክራሲ እና ከህዝባዊ መስመር የወጣ ኣስተሳሰብ ይዘን ስንጓዝ ስለነበርን ጥልቅ ተሃድሶ ያስፈልገናል’ ማለታቸውን ይታወሳል። ጥልቅ ተሃድሶው እወነትነት የሚኖረው በየድርጅቱ ያሉ ጥፋተኞችን ወደ ህግ ሲቀርቡ፣ ሲጠየቁ እና ከስልጣናቸው ሲሰናበቱ ብቻ ነው። በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ክልል የላይኛውን እና መካከለኛውን ኣመራር እስከመቀየር እና ተጠያቂ ለይቶ እስከ ማውጣት የደረሰ ሲሆን ብኣዴን ግን የጥፋቱ የሰላ ጫፍ የሆኑ፣ በክልሉ ታጣቂ ሃይሎች እንዲቀሳቀሱ የፈቀዱ፣ ትጥቅ ያስታጠቁ፣ ኣመጹን የመሩና የተሳተፉ የኣመራር ኣባላት ኣሁንም ስልጣን ላይ ናቸው። ይህ ባልተቀየረበት ሁኔታ ኢህኣዴግ እንደ ድርጅት ታድሶ ወደ ተሻለ መንገድ ይሄዳል ብሎ መገመት የዋህነት

ነው። የተጀመረውን ልማት ማስቀጠል እና ዳር ማድረስም እጅግ ኣስቸጋሪ ይሆናል። በኢህኣዴግ ኣባል ድርጅቶች ያለውን ግንኙነት በዚህ ከቀጠለ ደግሞ ኣደጋው ኣይጣል ነው።

**በመጨረሻ**

***ለብኣዴን*** - "በተሳሳተ መረጃ ላይ ተሞርኩዘን እህት ድርጅትን ጠርጥረነው ነበር ...፣ በጸረ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ ተበላሽተን ነበር ... " ወዘተ ብሎ ራሱን የገመገመው ብኣዴን ያ የተሳሳተ መረጃ ያለውን ለማረም የሰራው ስራ የለም። ብዚህ የተሳሳተ መረጃ ላይ ተመርኩዞ የያዘውን ኣቋም ከራሱ ኣልፎ ኣባሎቹ እና ተከታዮቹ ከማሳሳቱም በላይ የነዛውን መሰረተቢስ ወሬ ለፅንፈኛው ሃይል ተጨማሪ ግብኣት በመሆን እያገለገለ ይገኛል። በውጤቱ ደግሞ የትግራይ ህዝብ ተጠቅቶበታል ኣሁንም እየተጠቃበት ነው። ብኣዴን ሂስ ከማድረግ ያለፈ ጥፋቴ ብሎ ያመነውን በማረምና እንዲሁም የትግራይ ህዝብ በኣደባባይ ይቅርታ በመጠየቅ እና ለተፈናቀሉ፣ ለተዘረፉ፣ ንብረት ለወደመባቸው ወገኖችን እና ለጠፋው ሂወት ተገቢ ፍርድ እና ካሳ በመስጠት ታሪኩን ያስተካክል ዘንድ ወኔው ሊኖረው ይገባል። የእስከኣሁኑ ሳይበቃ ኣሁንም እየተሄደበት ያለው የጥፋት መንገድ ከማንም በላይ የሚጎዳው ቢኖር ብኣዴን እና ተከታዮቹ እንደሆነ ቆም ብለው ሊያስቡበት ይገባል። "Fool me once, shame on you; fool me twice, shame on me" እንደሚባለው የትግራይ ህዝብ ከኣሁን በኃላ ኣይሞኝም።

***ለህወሓት*** - መታወቅ ያለበት ነገር ቢኖር የፋሺሽቶቹ መንግስት ወድቆ በኣዲስ መንግስት ሲቀየር ህዝቡ የጓጓው ነገር ኣዲስ ባለስልጣናት ማየት ሳይሆን ኣዲስ እና በፊት ያጣውን ሁሉ የሚሰጠው ስርኣት ለመፍጠር ነበር። የትግራይ ህዝብ ሰላም፣ የተሻለ ስርኣት እና ለዘመናት ተነፍጎት የኖረውን ልማት እውን ለማድረግ ሲል የነበረውን የነፍጠኞች ስርኣት ለመገርሰስ ሁለንተናውን የከፈለ ህዝብ መሆኑን ለናንተ መንገር ለቀባሪ ማርዳት ይሆናል። ኋላ ቀረቹ የኣፄዎች መንግስታት እና ተከትሎ የመጣውን ፋሺሽታዊው ወታደራዊ መንግስት ከጫንቃው ለማውረድ በተደረገው የህዝቦች ትግል ትግራይ ከሌሎች በተለየ ሁኔታ የጦርነት ኣውድማ ሆና በመቆየትዋ ምክንያት 60 ሺ ወጣቶች የተሰዉባት፣ የሙቶ ሺ ታጋዮች ኣካል የጎደሉባት ብቻ ሳትሆን እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሲቪል ህዝብ በናፓልም ቦምብ የተጨፈጨፈባት፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ምሊሾች የተገደሉባት፣ እንስሳ፣ መንደሮች፣ እርሻ፣ የተፈጥሮ ሃብት የወደመባት፣ ረዳት ያጡ የሰማእታት ወላጆች ያሉባት፣ በኣስር ሺዎች የሚቆጠሩ ታጋዮች በባዶ እጅ ተሰናብተው የሚኖሩባት ክልል እንደሆነች ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ይህ በጦርነት የተንኮታኮተው ክልል እና ህዝብ በጦርነት የተጎዱ እና በተነፃፃሪ ልማት ወደ ኋላ የቀሩ ክልሎች የማገገሚያ ስራ ይሰራል የሚል የሽግግር መንግስት ወሬ ሳይጨበጥ የኤርትራ መንግስት ወረራ ደርሶ ክልሉ ለከፍተኛ ጉዳት ተዳርጓል። በፌደራል መንግስቱም የተደረገለት የማገገሚያ ድጎማ የለም።

የማገገሚያ ድጋፍ ማግኘት ይቅርና እንደማነኛውም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት የስርኣቱ ተጠቃሚ መሆን እየተገባ በመሪዎቹ ተገቢ ያልሆነ መሸማቀቅ፣ ክልልን ረስቶ የመሃል ኣገር ትኩረት ማድረግ፣ ቅጥ ያጣ ቸልተኝነት፣ ኣቅመቢስነት እና ሌሎች ኣሳሳቢ ችግሮች ምክንያት ክልሉ ኣሁን ባለበት ኣስከፊ ሁኔታ ላይ ደርሷል። ስለሆነም ኣሁን ያለውን የይሉኝታ ፖለቲካ ትግራይ እና ህዝብዋ ስለጎዳው ይህ ጎታች ባህል ከመሰርቱ ተነቅሎ መጣል ይኖርበታል። ህወሓት ስልጣን ላይ እስካለ እና መቀጠል የሚፈልግ ከሆነ የእስካሁኑ መንገድ ለራሱና ለህዝቡ የሚበጅ እንዳልነበረ ኣምኖ የኣካሄድ ስር ነቀል ለውጥ መድረግ ይጠበቅበታል። የማንም ሙብት እና ጥቅም ሳይነካ የህዝቡንና ክልሉን ጥቅም የሚያስከብር፣ የይሉኝታ ፖለቲካ ሰብሮ እንደ ኣሁኑ የትግራይ ወጣት እቅጩን የሚናገሩ መሪዎች እንዲኖሩት ይጠበቃል። የትግራይ ህዝብ ፋሺሽታዊ ስርኣት ለመገርሰስ ከማንም በላይ መስእዋት የከፈለው በማንም ትምክህተኞችና ዘረኞች ሊሸማቀቅ እና ጥቃት ሊደርስበት ሳይሆን ዘላቂ ጥቅሙን እና የማይሸራረፍ ሙብቱን ሊያስከብር መሆኖኑን ታውቆ ካለምንም ይሉኝታና መሸማቀቅ ጥቅሙን የሚያስከብርለት ፖለቲከኛ ይፈልጋል።

ሃዘንተኛ ክልል ይመስል በየኣመቱ እየመጡ የሚወራውን ያክል ያለመልማቱ የሚመሰክሩለት ጠያቂዎች የሚለግሱለትን ከንፈር መምጠጥ የትም ኣያደርሰውም። "ኣውቆ የተኛ ቢጠሩት ኣይሰማም" እንደተባለው ትግራይ ብትለማም ባትለማም የሚቀየር የጠላት ኣስተሳሰብ ኣይኖርም። መፍትሄው ያለመልማቱን ኣይተው የሚያዝኑለት ልቦች መፍጠር ወይም ኣሉባልታዎቹን የማከሸፍ ጥረት ሳይሆን የትግራይ ህዝብ ለጥቃት ተጋላጭ ያደረገው ሁኔታ በዘላቂነት መቀየርና ሁለንተናዊ ልማቱ ሲረጋገጥለት ብቻ ነው። ያኔ የሚነካው ኣይኖርም። ስለሆነም ህወሓት ኣሁን የተቀጣጠለውን የህዝቡ የመልማት ጥያቄ እና ለፀረ ህዝብ ሃይሎች ኣልበገር ባይነቱን በማድመጥ ህዝቡ በሚፈስበት ኣቅጣጫ ካልፈሰሰ በራሱ እየፈረደ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ህወሓት መሸማቀቅ ካለበት ትግራይን ባለማልማቱ እና ህዝቡን ከችጋር፣ ከስደት፣ ከስራ ኣጥነት፣ ከውሃ ጥም እና ሰላም በሌለበት ሁኔታ ህዝብ በመጎዳቱ ብቻ ነው።

***"ኣጋር ድርጅቶች"*** - በኢህኣዴግ ኣጠራር "ኣጋር" የሚባሉት የዓፋር፣ የሱማሌ፣ የሃረሪ፣ ጋምቤላ እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎችን እያስተዳደሩ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ለ27 ኣመታት በግልጽ ሲሰራበት የነበረውን የትምክህተኞች ሴራ ኣሁን የበለጠ ግልፅ ሆኖላቸዋል። በመሆኑም እነዚህ በእኩልነት መኖር ያልተዋጠላቸው ሃይሎች እየሄዱበት ያለው የጥፋት መንገድ በትግራይ ህዝብ ብቻ የሚቆም ኣለመሆኑን ተገንዝበ በንቃት ሊታገሉዋቸው ይገባል። እነዚህ ድርጅቶች በሚያስተዳድሩት ክልል ብቻ ሳይወሰኑ በፌደራል ስርኣቱ ሙሉ ተዋናይ በመሆን ተገቢ የትግል ድርሻቸው ሊወጡ ስለሚገባ ህገመንግስቱ በሚፈቅደው በፌደራል ተቋማት የሚገባቸውን ቦታ መጠየቅ ይኖርባቸዋል። ኢትዮጵያ የብዙ ብሄርና ብሄረሰቦች፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎች እና እምነቶች ኣገር መሆንዋን ተገንዝበው በእኩልነት መኖርን ሊለማመዱት የግድ ይላል። ይህ ያገጠጠ እውነታ የማይቀበል ካለ ሲሆን ስህተቱን ኣርሞ ይኑር ካልሆነ ግን መንገዱን ጨርቅ ያርግለት ሊሉት ይገባል። ህገ መንግስቱም ኣረጋግጦለታልና።

ሰላም!